## መመሪያ ቁጥር 907/2014
## በባህልና ስፖርት ሚኒስቴር

## ሀገር አቀፍ የስፖርት ማህበራት ስለሚቋቋሙበት ሁኔታ ለመወሰን ተሻሽሎ የወጣ መመሪያ

በሀገሪቱ የስፖርት ልማትና እድገት ውስጥ የሚሳተፍ የተለያዩ የስፖርት ማህበራትን አደረጃጀት፣ አሰራርና አመራር ተግባርና ኃላፊነት በግልጽ በማስቀመጥ ሰፊ መሠረት ያለው ህዝባዊ የስፖርት እንቅስቃሴ በማራመድና ህብረተሰቡን በማሳተፍ ውጤታማ የሆኑ ስፖርተኞችን ማፍራት አስፈላጊ በመሆኑ፣

በተለያዩ የስፖርት ዘርፎች የስፖርት ማህበራት ተመዝግበውና እውቅና አግኝተው ስፖርቱ እንዲያስፋፉና እንዲያሳድጉ ለማድረግ ተዘርግቶ የነበረውን የአሰራር ሥርዓት ፈትሾ በማስተካከል፣ የስፖርት ማህበራት በስፖርት ኢንቨስትመንት እና ፕሮሞሽን ሥራዎች ላይ በመሳተፍ ለዘርፉ እድገትና ለሀገር ኢኮኖሚ ድርሻቸዉን እንድያበረክቱ ለማድረግና የስፖርት አስተዳደር ፍትሃዊና ዲሞክራሳዊ በሆነ አግባብ የሚመራበትን ወጥ ስርዓት መቅረጽ በማስፈለጉ፣

ሚኒስቴሩ የፌደራል መንግስት አስፈጻሚ አካላትን ሥልጣንና ተግባር ለመወሰን በወጣው አዋጅ ቁጥር 1263/2014 አንቀጽ 37 1/ነ/ በተሰጠው ሥልጣን መሠረት ይህ መመሪያ አሻሽሎ አውጥቷል፡፡

## Directive no 907/2022
## Ministry of culture and sport

## Establishment of National Sport Associations

## Revised directive

WHEREAS, it is necessary to train effective athletes by promoting a broad-based mass sport and involving the community by clearly clarifying the organization, practices and responsibilities of various sport associations involved in the development and growth of sports in the country;

WHEREAS, it is necessary to establish a system in place to ensure that sport associations are registered and recognized in various sports sectors to promote and expand the sport in democratic way;

NOW THEREFORE, the Ministry as per article 37 (1) (n) of Proclamation No. 1263/2021 amended this directive as follows;

## ክፍል አንድ
## ጠቅላላ

1. **<u>አጭር ርዕስ</u>**

ይህ መመሪያ "ሀገር አቀፍ ስፖርት ማህበራት ስለሚቋቋሙበት ሁኔታ ለመወሰን ተሻሽሎ የወጣ መመሪያ ቁጥር 907/2014" ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል፡፡

2. **<u>ትርጓሜ</u>**

የቃሉ አገባብ ሌላ ትርጉም የሚያሰጠው ካልሆነ በስተቀር በዚህ መመሪያ ውስጥ፡-

1) **"ሚኒስቴር"** ማለት የባህልና ስፖርት ሚኒስቴር ነው፤
2) **"ዓለም አቀፍ ፌዴሬሽን"** ማለት በዓለም አቀፍ ደረጃ በየስፖርት ዓይነቱ የተቋቋሙ ፌዴሬሽኖችን ነው፤
3) **"ስፖርት ማህበራት"** ማለት አንድን ወይም የተለያዩ የስፖርት አይነቶችን ለመምራት፣ ለማስተባበርና ለመደገፍ የተደራጀ ህዝባዊ አደረጃጀቶችን የሚያጠቃልል ነው፤
4) **"ስፖርት ፌዴሬሽን"** ማለት አንድን ስፖርት አይነት በመላ አገሪቱ ለማስፋፋት፣ ለማሳደግና ለመምራት ከሚኒስቴሩ ፈቃድና ዕውቅና ተሰጥቶት የተቋቋመ የስፖርት ማህበር ነው፤
5) **"የኢትዮጵያ ኦሎምፒክ ኮሚቴ"** ማለት በዓለም አቀፍ የኦሎምፒክ ኮሚቴ ቻርተር መሠረት የኦሎምፒክ እንቅስቃሴን በመላ አገሪቱ ለማስፋፋት፣ ለማሳደግና ለመምራት ከሚኒስቴሩ ፈቃድና ዕውቅና ተሰጥቶት የተቋቋመ ኮሚቴ ነው፤
6) **"የኢትዮጵያ ፓራሊምፒክ ኮሚቴ"** ማለት በዓለም አቀፍ ፓራሊምፒክ ኮሚቴ ቻርተር መሠረት የፓራሊምፒክ ስፖርቶችን በመላው አገሪቱ ለማስፋፋት፣ ለማሳደግና ለመምራት ከሚኒስቴሩ ፈቃድና ዕውቅና ተሰጥቶት የተቋቋመ ኮሚቴ ነው፤

## PART ONE
## General

1. **<u>Short title</u>**

This directive may be cited as "establishment of national sport associations amended directive no 907/2022".

2. **<u>Definition</u>**

In this directive, unless the context requires otherwise:

1) "Ministry" means Ministry of Culture and Sport;
2) "International Federation" means federations established in their respective sport at the international level;
3) "Sport associations" means association established to direct, coordinate and support one or more sports at community level;
4) "Sport Federation" means a sport association established by the permission and recognition of the Ministry; to lead, develop and lead sport throughout the country;
5) "Ethiopian Olympic Committee" means a committee established with the permission and recognition of the Ministry, to promote and direct Olympic activities throughout the country in accordance with the International Olympic Charter;
6) "Ethiopian Paralympic Committee" means a committee authorized by the Ministry to promote, develop and lead Paralympic sports throughout the country in accordance with the International Paralympic Charter;

7) **"የኢትዮጵያ መስማት የተሳናቸው ስፖርቶች ፌዴሬሽን"** ማለት በዓለም አቀፍ ዲፍሊምፕክ ኮሚቴ ቻርተር መሠረት የኢትዮጵያ መስማት የተሳናቸው ስፖርቶች በመላ ሀገሪቱ ለማስፋፋት፣ ለማሳደግና ለመምራት ከሚኒስቴሩ ፈቃድና ዕውቅና ተሰጥቶት የተቋቋመ ማህበር ነው፤

8) **"የኢትዮጵያ ዩኒቨርሲቲዎች ስፖርት ማህበር"** ማለት በኢትዮጵያ ውስጥ በሚገኙ ዩኒቨርስቲዎች የሚመሰረት ሆኖ የተለያዩ የስፖርት አይነቶችን በዩኒቨርስቲዎች ውስጥ ለማስፋፋት፣ ለማሳደግና ለመምራት ከሚኒስቴሩ ፈቃድና ዕውቅና ተሰጥቶት የተቋቋመ ማህበር ነው፤

9) **"የኢትዮጵያ ማህበረሰብ አቀፍ የጤና ስፖርት ማህበር"** ማለት የማህበረሰብ አቀፍ የጤና ስፖርትን በመላ ሃገሪቱ ለማስፋፋት፣ ለማሳደግና ለመምራት ከሚኒስቴሩ ፈቃድና ዕውቅና ተሰጥቶት የተቋቋመ ማህበር ነው፤

10) **"ክልል"** ማለት በኢፌዲሪ ህገ መንግሥት አንቀጽ 47 መሰረት የተካተተ ማንኛውም ክልል ሲሆን የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደርና የድሬዳዋ አስተዳደርን ይጨምራል፤

11) **"የክልል ስፖርት ማህበር"** ማለት አንድን የስፖርት ዓይነት ወይም የተለያዩ የስፖርት ዓይነቶችን በክልሉ ለማስፋፋት፣ ለማሳደግና ለመምራት ከክልሉ አግባብነት ካለው አካል ፈቃድና ዕውቅና ተሰጥቶት የተቋቋመ ማህበር ነው፤

12) **"ታዋቂ የስፖርት ድርጅቶች"** ማለት የትምህርት ሚኒስቴር፣ የመከላከያ ሚኒስቴር፣ የጤና ሚኒስቴር፣ የኢትዮጵያ ፖሊስ ኮሚሽን፣ የፌዴራል ማረሚያ ቤት ኮሚሽን እና የኢትዮጵያ ሠራተኞች ማህበር ኮንፌዴሬሽን ማለት ሲሆን በስሩ የሚገኙ የስፖርት ልማት፣ ፌሲቲቫሎችና ውድድሮችን የሚያስተባብሩ አካላት ናቸው፤

7) "Ethiopian Deaf Sport Federation" means a federation established by the Permission of the Ministry to promote, develop and lead Ethiopian Deaf Sport in accordance with the International Deaflympics' Committee Charter;

8) "Ethiopian university's sport association" means an association established by the universities in Ethiopia with the permission and recognition of the Ministry to promote, develop and to lead various types of sports in the universities;

9) "Ethiopian Community Sport Association" means an association establish by the community with the permission and recognition of the Ministry to promote, develop and manage community sports throughout the country;

10) "Region" means any region established as per article 47 of the constitution and includes the Addis Ababa and Dire Dawa city administrations;

11) "Regional sport association" means an association established by the permission and recognition of the appropriate regional body for the promotion, development and navigation of one sport type or different sport types in the region;

12) "Prominent sport organizations" means the Ministry of Education, Ministry of Defense, Ministry of Health, Ethiopian Police Commission, Federal Prisons Commission and the Ethiopian Confederation of trade union;

13) **“የስፖርት ክለብ”** ማለት በአባላትና በስፖርተኞች ስብስብ ስፖርትን ለማራመድ ከስፖርት ማህበር ፈቃድ ተሰጥቶት የተቋቋመ ማህበር ነው፤

14) **“ጠቅላላ ጉባኤ”** ማለት የአንድ ስፖርት ማህበርን በበላይነት የሚመራ ከፍተኛው የስልጣን አካል ነው፤

15) **“ሥራ አስፈጻሚ ኮሚቴ”** ማለት አንድን ሀገር አቀፍ የስፖርት ማህበር የስራ እንቅስቃሴ በበላይነት ለማስፈጸም በማህበሩ ጠቅላላ ጉባኤ የተመረጠ አካል ነው፤

16) **“ስራ አስፈጻሚ ቦርድ”** ማለት የኢትዮጵያ ኦሎምፒክ ኮሚቴ ስራ አስፈጻሚ ቦርድ ነው፤

17) **“አባላት”** ማለት አንድን ስፖርት ማህበር የሚመሰርቱ ቀጥተኛ አግባብነት ያላቸው ማህበራት፣ ተቋማት ወይም ግለሰቦች ናቸው፤

18) **“አትሌት”** ማለት በአንድ ስፖርት ዓይነት ተመዝግቦ የሚወዳደር ወንድ ወይም ሴት ስፖርተኛ ነው፤

19) **“የምርጫ አስፈጻሚ ኮሚቴ”** ማለት በስፖርት ማህበሩ ጠቅላላ ጉባኤ የተሰየመ የማህበሩን ስራ አስፈጻሚ ኮሚቴ ምርጫ የሚያስፈጽም አካል ነው፤

20) **“የአትሌቶች ወኪል”** ማለት ከአለም አቀፍና ሃገር አቀፍ የስፖርት ማህበር ዕውቅና አግኝቶ ለአትሌቶች የውድድር ወይም የዝውውር እድል የሚያመቻች ግለሰብ ነው፤

21) **“የቡድን ስፖርቶች”** ማለት ከአንድ በላይ በሆኑ አትሌቶች በቡድን የሚካሄዱ የስፖርት ዓይነቶችን ነው፤

22) **“የአርት ስፖርቶች”** ማለት ወርልድ ቴኳንዶ፣ ኢንተርናሽናል ቴኳንዶ፣ ውሹ፣ካራቴ፣ ጁዶና ኪክ ቦክስ ወዘተ፤

13) "Sport Club" means an association licensed by the sport association to promote sports by members and sports teams;

14) "General Assembly" means the highest governing body of a sports association;

15) "Executive Committee" means a body elected by the General Assembly to oversee the activities of a national sports association;

16) "Executive Board" means the Executive Board of the Ethiopian Olympic Committee;

17) "Member" means direct associations, institutions or individuals who form a sports association;

18) "Athlete" means a male or female athlete who competes in a particular sport;

19) "Electoral Executive Committee" means the body that executes the election of the executive committee appointed by the general assembly of the sports association;

20) "Athletes' Agent" means a person who has been accredited by the International and National Sports Association to facilitate competition or transfer for athletes;

21) "Team sport" means sports played by a team of more than one athlete;

22) "Art Sports" means World Taekwondo, International Taekwondo, Wushu, Karate, Judo and Kick Boxing, etc.;

23) **"የግል ስፖርቶች"** ማለት አንድ አትሌት ብቻውን በግሉ የሚወዳደርበት የስፖርት ዓይነት ነው፤

24) **"ሰው"** ማለት የተፈጥሮ ሰው ወይም በህግ የሰውነት መብት የተሰጠው አካል ነው፤

25) ማንኛውም በወንድ ጾታ የተገለፀው አነጋገር የሴትንም ጾታ ይጨምራል፡፡

### 3. <u>የመመሪያው ዓላማ</u>

መመሪያው የሚከተሉት ዓላማዎች ይኖሩታል፡-

ሀ/ በሀገሪቱ የስፖርት ልማትና እድገት ውስጥ የሚሳተፍ የተለያዩ የስፖርት ማህበራትን አደረጃጀት፣ አሰራርና አመራር እንዲሁም ተግባርና ኃላፊነት በግልጽ ለማስቀመጥ፣

ለ/ በአገር አቀፍ ደረጃ የሚቋቋሙ የስፖርት ማህበራትን በመለየትና በመመዘን ተገቢውን እውቅናና ድጋፍ ለመስጠት ነው፡፡

### 4. <u>የተፈጻሚነት ወሰን</u>

ይህ መመሪያ ሀገር አቀፍ ስፖርት ማህበራት፣ ፓራሊምፒክ ኮሚቴ እና በኢትዮጵያ ኦሎምፒክ ኮሚቴ ላይ ተፈጻሚነት ይኖረዋል፡፡

## ክፍል ሁለት
## ስለ ሀገር አቀፍ ስፖርት ፌዴሬሽኖች

### 5. <u>የፌዴሬሽኖች ዓላማ</u>

እያንዳንዱ ሀገር አቀፍ የስፖርት ፌዴሬሽን የሚከተለው የጋራ ዓላማ ይኖራቸዋል፡፡

ሀ) ከተለያዩ ባለድርሻ አካላት ጋር በመተባበር የዘር፣ የፆታ፣ የቀለም፣ የሃይማኖት፣ የፖለቲካ ወይም ማናቸውም ልዩነት ሳያደርግ ስፖርቱን በመላ አገሪቱ ማስፋፋትና ውጤታማ ማድረግ፤

23) "Personal sport" is a sport in which an athlete competes alone;

24) "Person" means any natural or juridical person;

25) Any expression in the masculine gender includes the feminine.

### 3. <u>Objective of the directive</u>

The objectives of this directive is:

a) To clarify the organization, operation and management of various sports associations involved in the development and growth of sports in the country;

b) To identify sports associations to be established at the national level and provide appropriate recognition and support.

### 4. <u>Scope of application</u>

This directive applies to national sports associations, the Paralympic Committee and the Ethiopian Olympic Committee.

## PART TWO
## About National Sport Federations

### 5. <u>Objective of Federations</u>

All federations have to satisfy the following common objectives:

a) In collaboration with different stakeholders to promote and make effective sports all over the country without any discrimination on the basis of race, gender, color, religion, political outlook or any other reasons;

ለ) አገር አቀፍና ዓለም አቀፍ የስፖርት ህጎች፣ ደንቦችና መመሪያዎች በሀገሪቱ እንዲታወቁ፣ እንዲከበሩና ሥራ ላይ እንዲውሉ በማድረግ የስፖርቱን ህልውና ማስጠበቅ ነው፡፡

## 6. <u>የስፖርት ፌዴሬሽን ስያሜ</u>

ሀገር አቀፍ የስፖርት ፌዴሬሽኖች የሚከተለው አደረጃጀትና ስያሜ ይኖራቸዋል፡፡ በአገር አቀፍ ደረጃ በአንድ የስፖርት ዓይነት የሚቋቋም የስፖርት ፌዴሬሽን ኢትዮጵያ የሚል ስም በማስቀደምና የስፖርቱን ስም በመጥቀስ **"ፌዴሬሽን"** የሚል ስያሜ ይኖረዋል፡፡

## 7. <u>ፌዴሬሽን ለማቋቋም የሚያበቁ መስፈርቶች</u>

ሀገር አቀፍ የስፖርት ፌዴሬሽን ለመመስረትና ህጋዊ ዕውቅና ለማግኘት የሚከተሉት መመዘኛዎች መሟላት ይኖርበታል፡-

1/ በሀገሪቱ ስፖርቱን ለማስፋፋት በተቋቋመበት ስፖርት ብቸኛ አላማ ያለው መሆኑ ሲረጋገጥ፤

2/ ከሀገር አቀፍ የስፖርት ማህበራት መቋቋሚያ መመሪያ፣ ዓለም አቀፍ ደንብና የዲሞክራሲ መርህዎችን ጋር የተናበበ የራሱ የሆነ ግልጽ መቋቋሚያ ደንብ መኖሩ ሲረጋገጥና መመስረቻ ጽሁፍ ማቅረብ ሲችል፤

3/ ቢያንስ በ5 ክልሎች በፌዴሬሽን ደረጃ የተደራጁ ማህበራት መኖራቸውን ሲረጋገጥ፤

4/ በቡድን ስፖርት ተደራጅተው በክልሉ ዕውቅና ተሰጥቷቸው ቢያንስ ከ5 ያላነሱ ክለቦች ሲኖራቸው፤

5/ በአርት ስፖርቶች ቢያንስ በ2ኛ ዳን ደረጃ የሚያሰለጥኑ 5 የስልጠና ማዕከላት በክልሉ ሲኖራቸው፤

6/ በግል ስፖርቶች በክልል የተመዘገቡ ቢያንስ 150 ስፖርተኞች ሲኖራቸው፤

b) Securing/safeguarding the fate of the sport by means of ensuring the compliance of the international and national laws, rules and regulations throughout the country.

## 6. <u>Naming of Sport Federations</u>

National Sport Federations shall have the following Administrative structure and naming: A Federation organized on a specified sport at the National level will have a naming begins by the word “Ethiopia” and followed by the sports name and ends with the term “Federation”

## 7. <u>Requirements to Establish Federation</u>

To establish a national Federation with legal recognition the following requirements should be fulfilled:

1/ When it is the only established body with set of goals to promote the sport in country;

2/ When having memorandum of association and article of establishment issued inconsistent with this directive, international laws and principles;

3/ When federations are established at least in 5 regions;

4/ When at least 5 clubs in team sport are legally established in region;

5/ When At least 5 training centers that offer at 2nd dan level in art sports are established in the region;

6/ When 150 registered Athletes exists in the region in individual sports;

7/ በአገር አቀፍ ደረጃ ፌዴሬሽኑ የሚያወዳድራቸው ቢያንስ 6 ክለቦች በቡድን ስፖርቶች፣ 10 የስልጠና ማዕከላት በአርት ስፖርቶች እንዲሁም 250 የተመዘገቡ ስፖርተኞች በግል ስፖርቶች መኖራቸው ሲረጋገጥ፤

8/ በአገር አቀፍ ደረጃ ውድድሮችን ለመምራት የሚችሉ ቢያንስ ከ15 ያላነሰ ዳኞች እና አሰልጣኞች ያላቸው መሆኑ ሲረጋገጥ፤

9/ የስፖርት ማዘውተሪያ ስፍራዎች በስጦታ ወይም በትውስት ወይም በኪራይ ያሏቸው መሆኑ ሲረጋገጥ፤

10/ የስፖርት ልማት ፕሮግራም መኖሩ ሲረጋገጥ፤

11/ በስፖርት ማህበሩ ደረጃውን የጠበቀ ለውድድርና ስልጠና አገልግሎት የሚውል የስፖርት ቁሳቁስ መኖሩ ሲረጋገጥ፤

12/ የሂሳብ አያያዝን ሥርዓት የዘረጋ እና ኦዲትን በስራ ላይ የሚያውል መሆኑ ሲረጋገጥ፤

13/ ጽሕፈት ቤትና የሰው ሃይል መኖሩ ሲረጋገጥ ይሆናል፡፡

7/ When the National Federation owns at least 6 clubs in team sport competing at national level, 10 training centers in art sports, and 250 registered athletes for individual sports;

8/ When it has at least 15 competent referees and Coaches to lead competitions at the national level;

9/ When it has sport facilities through loan, donation or rent;

10/ When it has sport development Program;

11/ When it has standardized Sport equipment for competition and Training;

12/ When it has established financial management and auditing system;

13/ When it has its Own Secretariat office and necessary Human resource.

## 8. <u>የሀገር አቀፍ ስፖርት ፌዴሬሽን ስልጣንና ተግባር</u>

ሀገር አቀፍ የስፖርት ፌዴሬሽኖች የሚከተለው ስልጣንና ተግባር ይኖራቸዋል፡፡

1) የስፖርት ፖሊሲ፣ ስትራቴጂ፣ ፕሮግራም፣ አገር አቀፍና ዓለም አቀፍ ሕጎች፣ ደንቦችና፣ መመሪያዎች እንዲታወቁ፣ እንዲከበሩና እንዲተገበሩ ማድረግ፤
2) የማህበሩን ደንብና መመሪያዎችን የማውጣትና ሥራ ላይ እንዲውሉ ማድረግ፤
3) የስፖርት ክለቦች ስለሚደራጁበት ሁኔታ መመሪያ የማውጣትና ተግባራዊ እንዲሆን ማድረግ፤

## 8. Powers and Duties of the National Sport Federation

The National Sport Federations shall have the following powers and duties:

1) To enforce, respect and publicize Sport Policy, strategy, program, national and International rules and regulations;
2) To design and implement the Sport federations rules and regulations;
3) To issue directive regarding the organization of sport clubs and implementing the same;

4) በአገር አቀፍ፣ በአህጉር አቀፍና በዓለም አቀፍ ደረጃ በሚዘጋጁ ውድድሮች ለሚሳተፉ አካላት ፈቃድ መስጠት፤

5) ኢትዮጵያ ያፀደቀቻቸውን የፀረ ዶፒንግ ኮንቬንሽን እንዲታወቅና እንዲተገበር የማድረግ፤ በህጎቻቸው የአበረታች ቅመሞችን አካተው የማውጣትና በስፖርት አበረታች ቅመሞች ዙሪያ በሚደረገው ምርመራና ቁጥጥር አስፈላጊውን ትብብር የማድረግ፤

6) በስፖርት አበረታች ቅመሞች ዙሪያ አስፈላጊውን የትምህርትና ስልጠና የህዝብ ንቅናቄ ስራዎችን ማከናወን፤

7) በሚመራው ስፖርት የሚነሱ ማንኛውም ክሶችና አቤቱታዎችን መርምሮ ውሳኔ መስጠት፤

8) ስፖርታዊ ጨዋነት እንዲሰፍን የስፖርታዊ ጨዋነትና የሥነ-ምግባር መርሆዎች እንዲታወቁ ማስተማርና ተጥሶ ከተገኘ ተገቢውን የማስተካከያ እርምጃ መውሰድ፤

9) የተቋቋመበትን ስፖርት በሀገር አቀፍ ደረጃ የመምራት፣ የማስፋፋትና የማሳደግ፤

10) የክልል ስፖርት ፌዴሬሽኖችን በፋይናንስ፣ በቴክኒክና በስልጠና የመደገፍ፣

11) ደረጃቸውን የጠበቁ የስፖርት ማዘውተሪያ ስፍራዎችንና ማበልጸጊያ ማዕከላትን ማቋቋምና እንዲስፋፉ ማድረግ፤

12) ዘመናዊ የሥልጠና ሥርዓት በመዘርጋት ምርጥ ስፖርተኞችንና የተለያዩ ባለሙያዎችን በብዛትና በጥራት ማፍራት፤

13) ከአህጉራዊና ዓለም አቀፍ የስፖርት ተቋማት ጋር በመተባበር የተለያዩ ኮርሶችን፣ ሴሚናሮችን፣ ወርክሾፕንና ስልጠናዎችን በአገር ውስጥ ማዘጋጀትና መተግበር እንዲሁም በውጭ አገር በሚዘጋጁ ላይ መሳተፍ፤

4) To give permission for pertinent participants that engage on national, continental and international competitions;

5) To publicize on the doping laws ratified by Ethiopia, incorporating the doping issues in their directives and cooperating on the investigation of doping test;

6) To lead, promote and develop the at the national level;

7) To conduct education and public mobilization on doping issue;

8) To give decision on compliance and grievances of spot submitted to it;

9) To pronounce fair play and take necessary measure when an infringement occurs;

10) To give support for regional sport federations technically and financially;

11) To establish and promote standardized sport facility and training centers;

12) To develop elite athlete and sport professionals;

13) To prepare and participate on workshops, seminars, trainings designed in collaboration with continental and international sport institutions;

14)የአሰልጣኞችን፣ የዳኞችንና የስፖርተኞችን የማሠልጠኛ ማንዋል ማዘጋጀት፣ደረጃ ማውጣት፣ፈቃድ መስጠትና፣ መመዝገብ፤

15)ለብሔራዊ ቡድን አባላት የህይወት እና የአካል ደህንነት ዋስትና /ኢንሹራንስ/ የመግባት፤

16)የዓለም እና የሀገር አቀፋዊ መመሪያን መሠረት በማድረግ የማህበሩን የሥነ-ምግባር ደንብና የምርጫ ማስተግበሪያ ማውጣት፤

17)ስፖርቱ የሚያድግበትንና የሚስፋፋበትን ሁኔታ ለማመቻቸት ጥናት እንዲሁም የምርምር ስራዎችን የማከናወንና በዘርፉ የሚካሄዱ የጥናትና የምርምር ሰራዎችን መደገፍ፤

18)የተለያዩ ውድድሮችን በሀገር ደረጃ የማዘጋጀትና ለሚያዘጋጁ አካላት ፈቃድ የመስጠት፤

19)ሀገርን የሚወክሉ ምርጥ ስፖርተኞችን በማዘጋጀት በአህጉር አቀፍና በዓለም አቀፍ ውድድሮች ማሳተፍ፤

20)የፌዴሬሽኑን የተለያዩ መረጃዎች በአግባቡ እንዲያዙ፣ እንዲጠበቁና ለህብረተሰቡ ተደራሽ እንዲሆኑ ማድረግ፤

21)የፌዴሬሽኑን ስትራቴጂ ዕቅድ የማዘጋጀትና ተግባራዊ ማድረግ፤

22)ዓመታዊ ዕቅድና ሪፖርት የማዘጋጀትና ለጠቅላላ ጉባኤ ማቅረብ፤

23)በዓመት አንድ ጊዜ የፌዴሬሽኑን መደበኛ ጠቅላላ ጉባኤ ማካሄድ፤

24)የተለያዩ የገቢ ማስገኛ ስልቶችን በመቀየስና በመተግበር የፌዴሬሽኑን የፋይናንስ አቅም ማጎልበት፤

14) To prepare training manuals for coaches, referees and professionals, set standard and give license for them;

15) To inter life and physical insurance contract for the national team member;

16) To issue and implement ethical and electoral directives inconformity with national and international laws and principles;

17) To Facilitate, Perform and promote research works in order to improve and develop the Sport;

18) To Organize competitions at national level or license sport event organizers;

19) To Prepare elite national Athletes representing at the continental and International Level

20) To Safeguard the Documents and information of the federation and disseminate properly;

21) To Prepare and Implement the Federations' Strategic plan;

22) To Prepare, report and present the annual plan to the General Assembly;

23) To conduct the general Assembly meeting once in a Year;

24) To Increase financial status through implementing and probing variety of income generation strategies;

25)የፌዴሬሽኑ ጽ/ቤት በተገቢው የሰው ኃይልና በዘመናዊ መገልገያዎች ማደራጀት፤

26)ሌሎች የፌዴሬሽኑን ዓላማዎችን የሚያስፈጽሙ ተግባራትን የማከናወን ይሆናል፡፡

27)አስፈላጊ ሆኖ ሲገኝ አስቸኳይ ጠቅላላ ጉባኤ የመጥራት፡፡

## 9. <u>የሀገር አቀፍ ስፖርት ፌዴሬሽን አባላት</u>

የሀገር አቀፍ የስፖርት ፌዴሬሽኖች የሚከተሉት አባላት ይኖራቸዋል፡፡

1) የክልል ስፖርት ፌዴሬሽኖች፤
2) በሀገር አቀፍ ደረጃ ፌዴሬሽኑ መዝግቦ በአባልነት በመያዝ የሚያወዳድራቸው ክለቦች፤

## 10. <u>የሀገር አቀፍ ስፖርት ፌዴሬሽን ጠቅላላ ጉባኤ አባላት ስብጥር</u>

የሀገር አቀፍ ፌዴሬሽኖች ጠቅላላ ጉባኤ የሚከተለው ስብጥር ይኖራቸዋል፡፡

1/ የክልል ስፖርት ፌዴሬሽን ተወካዮች፤ /በድምጽ/፣

2/ የፌዴሬሽኑ ፕሬዚዳንትና ሥራ አስፈጻሚ ኮሚቴ አባላት፤ /በመደበኛ ስብሰባ ወቅት በድምጽ/፣ በምርጫ ጊዜ፤/ያለ ድምጽ/፣

3/ በአገር አቀፍ ደረጃ በፌዴሬሽኑ በአባልነት የተመዘገቡ ክለቦች ተወካዮች/ በጠቅላላ ጉባኤ /በድምጽ/፤

4/ በስፖርቱ ዓይነቱ የተደራጁ የሙያ ማህበራት ተወካዮች፤/ ያለ ድምጽ/

5/ በጠቅላላ ጉባኤ የተመረጡ በመስኩ የሰሩ የክብር አባላት፤/ያለ ድምጽ/

6/ የኢትዮጵያ ኦሎምፒክ ኮሚቴ፤/ያለ ድምጽ/

25) To Organize the federations' secretariat Office with appropriate human resource and variety of modern technologies;

26) To Perform any other activities to meet the goals of the federation;

27) To Call up the general assembly meeting, when it is in need.

## 9. <u>Members of the National Sport Federation</u>

The National Sport Federations will have the following members:

1) Regional Sport Federations;
2) Registered Clubs of the national federation that compete at national level.

## 10. <u>Members of National Sport Federation General Assembly</u>

National Sport Federations General Assembly shall have the following members:

1/ Regional Sport Federations / With Vote/;

2/ President of the federation and executive committee members /with vote during ordinary meetings/ and without vote during election time;

3/ Representatives of national clubs registered by the Federation. (with vote at General Assembly);

4/ Representatives of sport specific professional associations/without vote/;

5/ Honorary members assigned by general assembly on the basis of their experience in the field (without voting right);

6/ Ethiopian Olympic Committee /without vote/;

7/ በጠቅላላ ጉባኤ የተመረጡ ኦዲተር፤/ያለ ድምጽ/

8/ በጠቅላላ ጉባኤ የተፈቀደላቸው ለስፖርቱ አስተዋጽኦ ያደረጉ ድርጅቶች፤ግለሰቦችና የብሄራዊ ቡድን ተጫዋች የነበሩ ስፖርተኞች፤/ያለ ድምጽ/

9/ የማህበረሰብ አቀፍ የጤና ስፖርት ማህበር ተወካይ፤/ያለ ድምጽ/

10/ የኢትዮጵያ ዩኒቨርሲቲዎች ስፖርት ማህበር ተወካይ፤ /ያለድምጽ/

11/ የፌዴሬሽኑ ጽ/ቤት ኃላፊ፤/ያለ ድምጽ/

12/ የክልል ስፖርት ፌዴሬሽን ጽ/ቤት ኃላፊ፤ /ያለ ድምጽ/

13/ የሚኒስቴሩ ተወካይ፤/ያለ ድምጽ/

14/የኢትዮጵያ ስፖርት ሳይንስ ባለሙያዎች ማህበር ተወካይ፤/ያለ ድምጽ/ ይሆናሉ፡፡

**11. <u>ስለ ሀገር አቀፍ ስፖርት ፌዴሬሽኖች ስራ አስፈጻሚ ኮሚቴ አባላት ምርጫ</u>**

የሀገር አቀፍ ስፖርት ፌዴሬሽኖች ስራ አስፈጻሚ ኮሚቴ አባላት የምርጫ ሂደት በሚከተለው ሁኔታ ይከናወናል፡፡

1/ የእጩ አቀራረብ

ሀ) ለስፖርት ፌዴሬሽን ሥራ አስፈጻሚ ኮሚቴ አባል መወዳደር የሚፈልግ ማንኛውም ግለሰብ በክልል ስፖርት ፌዴሬሽን በኩል ተወዳድሮ በእጩነት ይቀርባል፤

ለ) የክለብ አደረጃጀት ያላቸው የክልል ስፖርት ፌዴሬሽኖች በአገር አቀፍ ፌዴሬሽኑ ስር ተመዝግበው ከሚወዳደሩ ክለቦቻቸው ጋር በመሆን ተወዳዳሪዎችን መርጠው በፌዴሬሽኑ አቅራቢነት ለዕጩነት ያቀርባሉ፤

7/ Auditors elected by the General Assembly /without vote/;

8/ Organizations, individuals and retired national team players approved by the general assembly for their prominent contribution /without vote/;

9/ Representative of Community Sports Association /without vote/;

10/ Representative of the Ethiopian Universities Sports Association /without vote/;

11/ Federation’s secretariat office Head/without vote/;

12/ Regional Sport Federation secretariat Office, head /without vote/;

13/ Representative of the Ministry /without vote/;

14/ Representative of Ethiopian Sport Science Professionals Association /without vote/.

**11. <u>Election of National Sport Federations Executive Committee members</u>**

Election of Executive committee members shall follow the following procedures:

1/ Assignment of Candidate

a) Any candidate for the executive committee member shall be assigned respective regional Sport Federations;

b) Regional sports federations that have registered clubs elect and present candidates together with nationally registered club structure;

ሐ) የክልል ስፖርት ፌዴሬሽኞች ለፕሬዝዳንትነት 1 ለስራ አስፈጻሚ ኮሚቴ አባልነት 2 እጩዎችን ማቅርብ ይችላል፤

መ)የክልል ስፖርት ፌዴሬሽኖች ለፕሬዚዳንትነት እና ለስራ አስፈጻሚ ኮሚቴ አባልነት የሚያቀርቧቸውን ዕጪዎች በስፖርት ምክር ቤታቸው ሥራ አስፈጻሚ ኮሚቴ ታይቶና ተረጋግጦ አጠቃላይ መረጃ ለአገር አቀፍ ፌዴሬሽኑ ከ2 ወር በፊት መላክ አለባቸው፤

ሠ) አንድ ለሥራ አስፈጻሚ ኮሚቴ ለመወዳደር በክልል ስፖርት ፌዴሬሽን አማካኝነት ተመርጦ በዕጩነት የቀረበ ተወዳዳሪ ከውድድሩ ራሱን ማግለል ከፈለገ ምርጫው ከመካሄዱ ከሶስት ሳምንት በፊት ለፌዴሬሽኑ ጽ/ቤት በጽሁፍ ማቅረብ አለበት፤

ረ) የአንድ ክልል ስፖርት ፌዴሬሽን ለሥራ አስፈጻሚ ኮሚቴ አባልነትም ሆነ ፕሬዚዳንትነት በዕጪነት እንዲቀርብ አወዳድሮ ያቀረበውን ዕጩ ተወዳዳሪ ማንሳት ቢፈልግ ለፌዴሬሽኑ ጽ/ቤት ከአንድ ወር በፊት ማሳወቅ አለበት፤

ሰ) የክልል ስፖርት ፌዴሬሽኖች በሚያቀርቧቸው ዕጪዎች መካከል 50% ሴቶችን ያሳተፈ መሆን አለበት፡፡

2/ ስለምርጫ አፈጻጸም ሂደት

ሀ) ምርጫው እያንዳንዱ ፌዴሬሽን ከዓለም አቀፉ ፌዴሬሽኑ ጋር አገናዝቦ በሚያወጣው የምርጫ ደንብ መሰረት ይከናወናል፡፡

ለ) የሥራ አስፈጻሚ ኮሚቴ ምርጫ የሚከናወነው በገለልተኛ የምርጫ አስፈጻሚ ኮሚቴ አማካኝነት ይሆናል፤

ሐ) ጠቅላላ ጉባኤው የፌዴሬሽኑን ፕሬዚዳንት፣ ተቀዳሚ ምክትል ፕሬዚዳንት፣ ምክትል ፕሬዚዳንት፣ እና ሌሎች ሥራ አስፈጻሚ ኮሚቴን አባላትን ይመርጣል፤

c) Regional sports federations present 1 candidate for the presidency and 2 candidates for the executive committee membership;

d) Candidates for the executive committee and presidency Presented by the regional federation shall be submitted with all the necessary documents before two months after the approval of the respective regional sport council executive committee;

e) If the executive committee Candidate seeks to withdraw from competition, he must apply to the federations' office in written 3 weeks before the Election;

f) If a regional sport federation seeks to cancel a candidate presented for national federations presidency or executive committee member, it shall notify before one month to the federation's secretariat office;

g) 50% of Regional federations' candidates should be women.

2/ Election Procedure

a) The election will be held according to respective federations electoral directives in conformity with the of the international laws and principles;

b) Executive Committee members' election shall be regulated by an independent election committee;

c) General Assembly will elect the federation president, first vice president, vice president and other executive committee members;

d) Election Committee should immediately announce the elected executive committee

መ) የምርጫ አስፈፃሚ ኮሚቴ በእለቱ የተመረጡ የስራ አስፈፃሚ ኮሚቴ አባላት ለጠቅላላ ጉባኤ ወዲያውኑ ማሳወቅ አለበት፤

ሠ) በስፖርት ፌዴሬሽኑ የተመረጡ የሥራ አስፈጻሚ ኮሚቴ አባላት ስም ዝርዝርና የስራ ኃላፊነት ለሚኒስትሩ እና ለሚመለከታቸው አካላት በጽሕፈት ቤቱ አማካኝነት ማሳወቅ አለበት፤

ረ) በቀድሞ እና በአዲስ በተመረጡ የሥራ አስፈጻሚ ኮሚቴ አባላት መካከል የርክክብ ሥርዓት በአንድ ሳምንት ጊዜ ውስጥ መከናወን አለበት፡፡

3/ ድምጽ አሰጣጥ

ሀ) የክልል ስፖርት ፌዴሬሽኖች ሁለት ሁለት ድምጽ ይኖራቸዋል፤

ለ) በሀገር አቀፍ ፌዴሬሽኑ ተመዝግበው በውድድር የሚሳተፉ ክለቦች አንድ አንድ ድምጽ ይኖራቸዋል፤

ሐ) በመደበኛ ዓመታዊ ጠቅላላ ጉባኤ ላይ የፌዴሬሽኑ ሥራ አስፈጻሚ ኮሚቴ አባላት አንድ አንድ ድምጽ ይኖራቸዋል፤

መ) የስራ ዘመናቸውን የጨረሱ የስራ አስፈፃሚ ኮሚቴ አባላት በምርጫ ጊዜ ድምፅ የላቸውም፤

ሠ) በጠቅላላው ጉባኤ አብላጫ ድምጽ ያመጣ ተመራጭ ሲሆን ስፖርት ማህበሩ ከዓለም አቀፉ ማህበሩ ጋር አገናዝቦ በሚያወጣው የምርጫ ህግ መሰረት የሚፈጸም ይሆናል፤

ረ) ድምጽ የሚሰጠው ሚስጥራዊ በሆነ መንገድ ነው፡፡

## 12.<u>የኢትዮጵያ ኦሎምፒክ ኮሚቴ ዓላማ</u>

የኢትዮጵያ ኦሎምፒክ ኮሚቴ የሚከተለው ዓላማ ይኖረዋል፤

በኦሎምፒክ ቻርተርና በሃገሪቱ የስፖርት ፖሊሲ፣ ህጎች ደንቦችና መመሪያ መሰረት የኦሎምፒክ ፍልስፍናንና ጽንሰ ሃሳብ በሃገሪቱ በማስረጽ የኦሎምፒክ ንቅናቄን ማዳበር፣ ማራመድ እና መጠበቅ ነው፡፡

members to the general assembly;

e) Secretariat office of the federation should announce list of elected executive committee members and their responsibility to the ministry and other responsible bodies;

f) Within one-week time Transition between the previous and newly elected executive committee members shall be finalized.

3/ Voting

a) Each Regional Sport Federation has two votes;

b) Each club registered and compete by the national federation has one vote;

c) Each federation executive committee members have one vote at ordinary annual general assembly meeting;

d) During Election time; members of the executive committee whose terms have lapsed have no vote;

e) Candidate that obtains majority vote on the general assembly shall assume the position, details of election procedure will have designed by the committee in line with international association;

f) The vote is conducted by secret ballot.

## 12. <u>Ethiopian Olympic Committee Objective</u>

The Ethiopian Olympic Committee shall have the following goals:

To educate, promote and reserve the philosophy of Olympics in Conformity with the Olympic charter, the national sport policy, rules and regulations.

## 13. <u>የኢትዮጵያ ኦሎምፒክ ኮሚቴ ማቋቋሚያ መስፈርት</u>

የኢትዮጵያ ኦሎምፒክ ኮሚቴን ለማቋቋምና ህጋዊ ዕውቅና ለማግኘት የሚከተሉት መመዘኛዎች መሟላት ይኖርበታል፡፡

1) በኦሎምፒክ ቻርተር መሰረት የኦሎምፒክ ፍልስፍና ለማራመድ በሀገሪቱ ብቸኛ መሆኑ ሲረጋገጥ፤
2) የዓለም አቀፍ ኦሎምፒክ ኮሚቴ ቻርተር እና ይህን መመሪያ መሰረት ያደረገ በጠቅላላ ጉባኤው የፀደቀ የራሱ መተዳዳሪያ ደንብ መኖሩ ሲረጋገጥና መመስረቻ ፅሁፍ ማቅረብ ሲችል፤
3) የዓለም አቀፍ ስፖርት ፌዴሬሽን አባል የሆኑ ስፖርታቸው በኦሎምፒክ ስፖርት የተመዘገቡ ቢያንስ 5 አገር አቀፍ ፌዴሬሽኞች መኖራቸው ሲረጋገጥ፤
4) የራሱ የሆነ አካውንት ያለው መሆኑ ሲረጋገጥ
5) የተደራጀ ጽሕፈት ቤትና የሰው ኃይል መኖሩ ሲረጋገጥ፣

## 14. <u>የኢትዮጵያ አሎምፒክ ኮሚቴ ስልጣንና ተግባር</u>

የኢትዮጵያ ኦሎምፒክ ኮሚቴ የሚከተሉት ስልጣንና ተግባራት ይኖሩታል፡፡

1) የሀገሪቱ ስፖርት ፖሊሲ፣ ስትራቴጂ፣ ፕሮግራም፣ ህጎች፣ ደንቦችና መመሪያዎች ተግባራዊ ማድረግ፤
2) በኦሎምፒክ ቻርተር እና በዓለም አቀፍ ኦሎምፒክ ኮሚቴ በወጡ ህጎች እና

## 13. <u>Requirements for Ethiopian Olympic Committee Establishment</u>

For the establishment of the Ethiopian Olympic Committee the following requirements shall be fulfilled:

1) When it is the only body to Promote Olympic Philosophy in line with the Olympic charter;
2) When it has article of association and establishment directives approved by general assembly in conformity with this directives and International Olympic committee charter;
3) When it has 5 Olympic sports federations which are members of their respective international federations;
4) When it has its own confirmed financial account;
5) When it has its own secretariat office and human resource.

## 14. <u>Duties and Responsibilities of the Ethiopian Olympic Committee</u>

The Ethiopian Olympic Committee has the following duties and responsibilities:

1) Implementing the national sport policy, strategy, programs, laws, rules and regulations;
2) Introducing, promoting and preserving the Olympic movements and values according to the Olympic charter and Olympic

መመሪያዎች መሠረት በሀገሪቱ የኦሎምፒክ እንቅስቃሴ መርሆዎችን ማዳበር፣ የማስተዋወቅና እና የመጠበቅ፤

3) ኢትዮጵያ ያፀደቀቻቸውን የፀረ ዶፒንግ ኮንቬክሽን እንዲታወቅና እንዲተገበር የማድረግ፤ በሚወጡ ህጎች የአበረታች ቅመሞችን አካተው የማውጣትና በስፖርት አበረታች ቅመሞች ዙሪያ በሚደረገው ምርመራና ቁጥጥር አስፈላጊውን ትብብር የማድረግ፤

4) በስፖርት አበረታች ቅመሞች ዙሪያ አስፈላጊውን የትምህርትና ስልጠናና የህዝብ ንቅናቄ ስራዎችን ማከናወን፤

5) በዓለም አቀፍ የፀረ-ዶፒንግ ህግ አንቀጽ 20 (4) ስር የተቀመጡ ተግባርና ኃላፊነቶችን የመፈጸም፤

6) የኦሎምፒክ መሰረታዊ መርሆዎችን እና እሴቶችን በአገሪቱ ለማሳደግና ለማስፋፋት የኦሎምፒክ ትምህርቶችን የሚሰጡ እንደ ኦሎምፒክ አካዳሚዎች፣ የኦሎምፒክ ሙዚየሞች እና ሌሎች ፕሮግራሞችን የሚያካሂዱ ተቋማትን የመደገፍ እና የማበረታታት፤

7) የኦሎምፒክ መሠረታዊ መርሆዎች እንዲስፋፉ ማድረግ የስፖርት ትምህርትና የስፖርት አስተዳደር ሥልጠናዎች እንዲሰጥ የመደገፍ፤

8) ስፖርተኞች በኦሎምፒክ ጨዋታዎች እና አህጉራዊና ዓለም አቀፋዊ ጨዋታዎች ሀገራችንን ወክለው እንዲሳተፉ ማስተባበር ድጋፍ መስጠት፤

9) የስፖርት ለሁሉም እንዲሳተፉና መደገፍና ማበረታታት፤

committee laws and principles;

3) Respecting and promoting the national Anti-doping laws, incorporating anti-doping issues by its directives and Cooperating to any movements of anti-doping investigation and testing;

4) Implementing the necessary Anti-doping education, training and campaigning;

5) Implement activities listed under the international anti-doping convention;

6) Assisting organizations working on promoting and developing the Olympic values through Olympic education (Olympic academies, Olympic Museums and other programs) in the country;

7) Promoting the Olympic values and supporting trainings related to sport education and administration;

8) Supporting and organizing Olympic sport athletes to represent their country at national and international games;

9) Promoting and Supporting to develop sport for all;

10) ውጤታማና ምርጥ አትሌቶችን የማፍራት ስራ እንዲጠናከር ማበረታታትና መደገፍ፤

11) ከአትሌቶች ህክምና እና ጤና ጋር በተያያዘ አስፈላጊውን ድጋፍ የማድረግ፤

12) በሀገሪቱ የስፖርት ማሰልጠኛ ማዕከልና የማዘውተሪያ ስፍራዎች እንዲስፋፉ ድጋፍ የማድረግ፤

13) ዓላማውን ለማሳካት መንግስታዊና መንግስታዊ ካልሆኑ ተቋማት ጋር በትብብር መስራት፤

14) በሚመራው ኦሎምፒክ ኮሚቴ የሚነሱ ማንኛውም ክሶችና አቤቱታዎችን መርምሮ ውሳኔ መስጠት፤

15) የስፖርት ልማቱን ሊደግፉ የሚችሉ ገቢ የማመንጨት ስራዎችን የማከናወን፣

16) ቢያንስ በዓመት አንድ ጊዜ ጠቅላላ ጉባኤ የካሂድ፤

17) ዓመታዊ እቅድና ወቅታ የስራ አፈጻጸም ሪፖርት ለሚኒስቴሩና ለሚመለከተው አካል የማቅረብ፤

18) ሌሎች ዓላማውን ለማስፈጸም የሚረዱ ተግባራትን ማከናወንን ያጠቃልላል፡፡

19) አስፋላጊ ሆኖ ሲገኝ አስቸኳይ ጠቅላላ ጉባኤ የመጥራት፡፡

## 15. <u>የኢትዮጵያ ኦሎምፒክ ኮሚቴ አባላት</u>

የኢትዮጵያ ኦሎምፒክ ኮሚቴ የሚከተሉት አባላት ይኖሩታል፡፡

1) በዓለም አቀፍ ስፖርት ፌዴሬሽን አባልነት የተመዘገቡ እና ስፖርቶቻቸው በኦሎምፒክ

10) Supporting and encouraging successful elite athletes' development;

11) Assisting athlete health and medical related issues;

12) Promoting the development of sport facility and training centers;

13) Cooperating with other governmental and non-governmental organizations to meet its objectives;

14) Making Decisions for any complaints and grievances raised under its Olympic committee;

15) Implementing and designing income generation and development programs;

16) Conduct general assembly meeting at least once in a year;

17) Prepare annual plan, work reports and submit to the ministry and responsible bodies;

18) Implement other duties to meet its objectives;

19) Call General assembly meeting when in need.

## 15. <u>Members of the Ethiopian Olympic Committee</u>

The Ethiopian Olympic Committee consists of the following members:

1/ National Olympic sport federations registered in their respective international

ፕሮግራም ውስጥ የተካተቱ አገር አቀፍ ፌዴሬሽኖች፤

2) ኢትዮጵያዊ የሆነ የዓለም አቀፍ ኦሎምፒክ ኮሚቴ አባል፤

3) ኢትዮጵያዊ የሆነ የአፍሪካ ኦሎምፒክ ኮሚቴ /ANOCA/ አባል፤

4) በኦሎምፒክ ጨዋታ ተሳትፎ ያቆሙ 2 የአትሌት ተወካዮች፡፡

## 16. <u>የኢትዮጵያ ኦሎምፒክ ኮሚቴ ጠቅላላ ጉባኤ ስብጥር</u>

የኢትዮጵያ ኦሎምፒክ ኮሚቴ በኦሎምፒክ ቻርተር አንቀጽ 28 የተጠቀሱትን አካቶ የሚከተሉት የጠቅላላ ጉባኤ ስብጥር ይኖረዋል፡፡

1/ በዓለም አቀፍ ስፖርት ማህበራት የተመዘገቡ እና ስፖርቶቻቸው በኦሎምፒክ ፕሮግራም ውስጥ የተካተቱ ሀገር አቀፍ የስፖርት ማህበራት ተወካዮች፤ /በድምጽ/

2/ ኢትዮጵያዊ ዜግነት ያለው የዓለም አቀፍ ኦሎምፒክ ኮሚቴ አባል፤ /በድምጽ/

3/ በዓለም አቀፍ ስፖርት ማህበራት የተመዘገቡና የታወቁ ስፖርቶቻቸው በኦሎምፒክ ፕሮግራም ውስጥ ያልተካተቱ ሀገር አቀፍ የስፖርት ማህበራት ተወካዮች፤/በድምጽ/

4/ ኢትዮጵያዊ ዜግነት ያለው የአፍሪካ ኦሎምፒክ ኮሚቴ ማህበር /ANOCA/ አባል /በድምጽ/

5/ የኦሎምፒክ ኮሚቴው ፕሬዚዳንትና ሥራ አስፈጻሚ ኮሚቴ ቦርድ አባላት፤/በድምጽ/

6/ በኦሎምፒክ ተሳትፈው ውድድር ያቆሙ አትሌቶች ከተሳተፉበት የመጨረሻው የኦሎምፒክ ጨዋታዎች በኋላ ከሦስት ኦሎምፒያድ (12 ዓመት) መጨረሻ ላይ የደረሱ አንድ ወንድና አንድ ሴት በማህበራቸዉ የሚወከሉ በአባልነት፤/በድምጽ/

federations;

2/ An Ethiopian citizen having membership title in International Olympic committee;

3/ An Ethiopian citizen having membership title in African Olympic Committee /ANOCA/ Member;

4/ Representatives of two Veteran Olympic Participant Athletes.

## 16. <u>Composition of Ethiopian Olympic Committee General Assembly</u>

According to the Olympic Charter; the Ethiopian Olympic Committee has the following compositions:

1/ Representatives of the National Olympic sport federations which are registered in their respective international federations, (with vote);

2/ An Ethiopian citizen having membership title in International Olympic committee, (With vote);

3/ Representatives of the Non-Olympic Sport National federations which are registered in their respective international federations, (with vote);

4/ An Ethiopian citizen having membership title in Africa Paralympic committee /ANOCA/, (with voting right);

5/ President of the Olympic Committee and executive committee members, (with voting right);

One male and one female Veteran Olympic participant athletes' representatives that had participated before three Olympics (12 years) and terminate competitions, (with Vote);

7/ በኦሎምፒክ ተሳትፈው በውድድር ላይ ያሉ አንድ ወንድ አንድ ሴት አትሌቶች በማህበራቸው የሚወከሉ፤ /በድምጽ/

8/ ታዋቂ የስፖርት ድርጅቶች ተወካዮች፤ /ያለ ድምጽ/

9/ የኢትዮጵያ ፓራሊምፒክ ኮሚቴ ተወካይ፤/ያለ ድምጽ/

10/የኢትዮጵያ ማህበረሰብ አቀፍ ጤና ስፖርት ማህበር ተወካይ፤/ያለ ድምጽ/

11/የኢትዮጵያ ኦሎምፒክ ኮሚቴ ኮሚሽኖች ተወካይ፤/ያለ ድምጽ/

12/በኢትዮጵያ ኦሎምፒክ ኮሚቴ ጠቅላላ ጉባኤ የተመረጡ የክብር አባላት /ያለድምጽ/

13/የኢትዮጵያ ኦሎምፒክ ኮሚቴ ዋና ፀሐፊ፤/ያለ ድምጽ/

14/በዓለም አቀፍ ስፖርት ማህበራት የተመዘገቡና ስፖርቶቻቸው በኦሊምፒክ ፕሮግራም ውስጥ የተካተቱ ሀገር አቀፍ የስፖርት ፌዴሬሽን ጽህፈት ቤት ኃላፊዎች፤/ያለድምጽ/

15/የኢትዮጵያ ዩኒቨርሲቲዎች ስፖርት ማህበር ተወካይ፤/ያለ ድምጽ/

16/የክልል ወጣቶችና ስፖርት ቢሮ ኃላፊ፤/ያለ ድምጽ/

17/ የሚኒስቴሩ ተወካይ /ያለ ድምጽ/

18/ የኢትዮጵያ ስፖርት ሳይንስ ባለሙያዎች ማህበር ተወካይ /ያለ ድምጽ/

**17.** <u>**የኢትዮጵያ ኦሎምፒክ ኮሚቴ ስራ አስፈጻሚ ቦርድ ምርጫ**</u>

የኢትዮጵያ ኦሎምፒክ ኮሚቴ ስራ አስፈጻሚ ቦርድ ምርጫ በሚከተሉት ሁኔታዎች ይመራል፡፡

7/ One Male and One Female Olympic Participant Athletes and currently engaged on competitions, (with vote);

8/ Known Sport company representatives, (without Vote);

9/ Representatives of the Ethiopian Para-lympic Committee members', (without vote);

10/ Representatives of the Ethiopian Com-munity sport Association, (without vote);

11/ Representatives of the Ethiopian Olympic Committee Commission, (without vote);

12/ Honorary members nominated by the Olympic committee general Assembly, (without vote);

13/ Ethiopian Olympic Committee General Secretariat, (without vote);

14/ General Secretariats of the Olympic Sports National federations which are registered in their respective international federations, (without vote);

15/ Representative of the Ethiopian Universities Sport Association, (without vote);

16/ Regional administration Sport bureau manager, (without vote);

17/ Representative of the ministry, (without vote);

18/ Representative of the Ethiopian Sport Science Professionals Association, (Without vote).

**17.** <u>**Election of Ethiopian Olympic Committee Executive Board**</u>

Election of the executive board follows the following Procedures:

1/ የእጩ አቀራረብ

ሀ/ ለኦሎምፒክ ኮሚቴ ሥራ አስፈጻሚ ቦርድ አባል መወዳደር የሚፈልግ ማንኛውም የአባል ፌዴሬሽን ፕሬዚዳንት በፌዴሬሽኑ አማካኝነት በእጩነት ይቀርባል፤

ለ/ የኦሎምፒክ ኮሚቴ አባል ፌዴሬሽን አንድ ዕጩ ተወዳዳሪ ለፕሬዚዳንትነት ወይም ለቦርድ አባልነት ለይቶ ያቀርባል፤

ሐ/ ሀገር አቀፍ ፌዴሬሽኖች ለፕሬዚዳንትነት ወይም ለስራ አስፈጻሚ ቦርድ አባልነት የሚያቀርቧቸውን ዕጪዎች አጠቃላይ መረጃ ለኦሎምፒክ ኮሚቴ ከ2 ወር በፊት መላክ አለባቸው፤

መ/ በሀገር አቀፍ ፌዴሬሽን አማካኝነት በዕጩነት የቀረበ ተወዳዳሪ ከውድድሩ ራሱን ማግለል ከፈለገ ምርጫው ከመካሄዱ ከሦስት ሳምንት በፊት ለኦሎምፒክ ኮሚቴው ጽ/ቤት በጽሁፍ ማቅረብ አለበት፤

ሠ/ ለኦሎምፒክ ኮሚቴ ሥራ አስፈጻሚ ቦርድ የሚቀርቡ ዕጪዎች መካከል 50% ሴቶችን ያሳተፈ መሆን አለበት፡፡

2/ ስለምርጫ አፈጻጸም ሂደት

በዚህ መመሪያ አንቀጽ 11 ን/አንቀጽ 2 ለሀገር አቀፍ ስፖርት ፌዴሬሽን የተደነገጉት የምርጫ አፈጻጸም ድንጋጌዎች በኢትዮጵያ ኦሎምፒክ ኮሚቴ ላይ ተፈጻሚ ይሆናል፡፡

3/ ድምጽ አሰጣጥ

ሀ) የኦሎምፒክ ስፖርት የሆኑ የሀገር አቀፍ ስፖርት ፌዴሬሽን ፕሬዚዳንቶች አንድ አንድ ድምጽ ይኖራቸዋል፤

ለ) የዓለም አቀፍ ኦሎምፒክ ኮሚቴ አባል የሆኑ አንድ ድምጽ፤

ሐ) የአፍሪካ ኦሎምፒክ ኮሚቴ አባል የሆኑ አንድ ድምጽ፤

1/ Candidate Assignment

a) Any president of member Federation that seeks to compete for Olympic Committee Presidential election shall be assigned by his respective federation;

b) Any member Federation can present only one candidate for each presidency and board membership;

c) National Federations shall send necessary documents of the assigned candidates before two months;

d) If the executive committee Candidate seeks to withdraw from competition, he must apply to the federations' office in written 3 weeks before the Election;

e) 50% of Regional federations' candidates should be women.

2/ Election Procedures

Article 11/ 2 of this directives shall also apply for Olympic Committee election:

3/ Voting Procedures

a) Presidents of the Olympic Sports Federations have one vote for each;

b) Members of the International Olympic committees have one vote;

c) Members of the African Olympic committees have one vote;

መ) በአለም አቀፍ ስፖርት ስፖርት ማህበራት የተመዘገቡና የታወቁ ስፖርቶቻቸው በኦሎምፒክ ፕሮግራም ውስጥ የተካተቱ አገር አቀፍ የስፖርት ማህበራት አንድ አንድ ድምጽ፤

ሠ) በኦሎምፒክ ውድድር ተሳትፈው ውድድር ያቆሙ የአትሌቶች ተወካይ አንድ አንድ ድምጽ፤

ረ) በኦሎምፒክ ተሳትፈው በውድድር ላይ ያሉ አንድ ወንድ እና አንድ ሴት አትሌት አንድ አንድ ድምጽ፤

ሰ) በመደበኛ ዓመታዊ ጠቅላላ ጉባኤ ላይ የኮሚቴው ሥራ አስፈጻሚ ቦርድ አባላት አንድ አንድ ድምጽ ይኖራቸዋል፤

ሸ) የስራ ዘመናቸውን የጨረሱ የስራ አስፈፃሚ ቦርድ አባላት በምርጫ ጊዜ ድምፅ መስጠት አይችሉም፤

ቀ) በጠቅላላው ጉባኤ አብላጫ ድምጽ ያመጣ ተመራጭ ሲሆን ስፖርት ማህበሩ ከዓለም አቀፉ ኮሚቴው ጋር አገናዝቦ በሚያወጣው የምርጫ ህግ መሰረት የሚፈጸም ይሆናል፤

በ) ድምጽ ሚስጥራዊ በሆነ መልኩ ይሰጣል፤

ተ) የኦሎምፒክ ሥራ አስፈጻሚ ቦርድ አባል የፌዴሬሽኑን አባልነት ወይም የወከለውን አካል ቢለቅ በኦሎምፒክ ኮሚቴ የሚኖረው አባልነት ይቋረጣል፡፡

## 18. የኢትዮጵያ ፓራሊምፒክ ኮሚቴ ዓላማ

የኢትዮጵያ ፓራሊፒክ ኮሚቴ የሚከተሉት ዓላማዎች ይኖረዋል፡፡

ሀ) የዘር፣ የፆታ የቋንቋ፣ የኃይማኖት፣ የፖለቲካ ልዩነት ሳይደረግና መድልኦ ሳይኖር የአካል ጉዳተኞች ኢትጵያውያን የሚሳተፉባቸውን

d) Representatives of the Non-Olympic National Sport federations which are registered in their respective international federations have one vote for each;

e) Representatives of the Veteran Olympic Participant Athletes have one vote;

f) Each Representatives of the Olympic Participant Active Athletes have one Vote;

g) Each Member of the executive committee on general Assembly meetings have one vote;

h) During Election time; members of the executive committee lapsed their terms have no vote;

i) Candidate that obtains majority vote on the general assembly shall assume the position, details of election procedure will have designed by the committee in line with international association;

j) The vote is conducted by secret ballot;

k) Olympic Executive Committee member loses membership if he leaves the member federation or representation.

## 18. Ethiopian Paralympic committee Objectives

The Ethiopian Paralympic committee has the following objectives:

a) Promote and make effective sports for people with disability all over the country without any discrimination on the basis of race, gender, color, religion, political

ስፖርቶች በመላ አገሪቱ በማስተዋወቅ፣ በማስፋፋት፣ በማሳደግና ውጤታማ በማድረግ ማህበረሰቡን ተሳታፊና ተጠቃሚ ማድረግ፤

ለ) የኢትዮጵያ ስፖርት ፖሊሲ፣ አገር አቀፍና ዓለም አቀፍ የስፖርት ህጎች፣ ደንቦች፣ መመሪያዎች በአገሪቱ እንዲታወቅና እንዲተገበር በማድረግ የስፖርቱን ህልውና ማስጠበቅ፤

**19. <u>የኢትዮጵያ ፓራሊምፒክ ኮሚቴ ማቋቋሚያ መስፈርት</u>**

የኢትዮጵያ ፓራሊፒክ ኮሚቴ ለማቋቋም የሚከተሉት መመዘኛዎች መሟላት ይኖርበታል፡-

1) በአለም አቀፉ ፓራሊምፒክ ህግጋት መሰረት የፓራሊፒክ ስፖርቶችን ለማስፋፋት በሀገሪቱ ብቸኛ መሆኑ ሲረጋገጥ፤
2) የዓለም አቀፍ ፓራሊምፒክ ኮሚቴ ደንብና ይህን የሀገር አቀፉን ስፖርት ማህበራት ማቋቋሚያ መመሪያ መሰረት ያደረገ፣ በጠቅላላ ጉባኤው የፀደቀ የራሱ መተዳደሪያ ደንብና መመስረቻ ጽሁፍ መኖሩ ሲረጋገጥ፤
3) በስፖርት ዓይነት ወይም በጉዳት ዓይነት የተቋቋሙ በሚኒስቴሩ ፈቃድ የተሰጣቸው ቢያንስ ከ4 ያላነሱ ሀገር አቀፍ ፌዴሬሽኖችን በአባልነት ያካተተ መሆኑ ሲረጋገጥ፤
4) ቢያንስ በ5 ክልሎች በፓራሊምፒክ ኮሚቴ ደረጃ የተደራጁ ማህበራት መኖራቸውን ሲረጋገጥ፤
5) የተደራጀ ፅ/ቤትና የሰው ኃይል መኖሩ ሲረጋገጥ፤

outlook or any other reasons;

b) Safeguarding the sports values and existence by means of ensuring the compliance of the international and national laws, rules and regulations throughout the country.

**19. <u>Requirements for Ethiopian Paralympic Committee Establishment</u>**

Requirements for Ethiopian Paralympic Committee establishments:

1/ When it is the only body existed to Promote Paralympic in line with the international Paralympic principles;

2/ When having memorandum of association and article of establishment issued inconsistent with this directive, international laws and principles;

3/ When it has at least 4 ministry licensed national federations classified by sports or disability type;

4/ When at least 5 regions established the Paralympic committee;

5/ When it has organized secretariat office and human resource;

6) ኮሚቴው የራሱ የሆነ አካውንት ያለው መሆኑ ሲረጋገጥ፤

## 20. <u>የኢትዮጵያ ፓራሊምፒክ ኮሚቴ ስልጣንና ተግባር</u>

የኢትዮጵያ ፓራሊምፒክ ኮሚቴ የሚከተሉት ስልጣንና ተግባራት ይኖሩታል፡፡

1/ የሀገሪቱን ስፖርት ፖሊሲ፣ ስትራቴጂ፣ ፕሮግራም፣ ሕግ፣ ደንቦችንና መመሪያዎችን ተግባራዊ ማድረግ፤

2/ የፓራሊምፒክ ስፖርታዊ እንቅስቃሴን በሀገር ውስጥ የማስፋፋትና የማሳደግ፤

3/ በአለም አቀፍና በሀገር አቀፍ ደረጃ በሚዘጋጀው የፓራሊምፒክ ስፖርት ጨዋታዎች የአካል ጉዳተኛውን ህብረተሰብ ተሳትፎ በማሳደግ ሀገራችንን ተጠቃሚ የማድረግ፤

4/ የፓራሊምፒክ ስፖርቶች በመላ ሃገሪቱ ስለሚስፋፉበትና ስለሚያድጉበት ሁኔታ ስልጠና መስጠትና ምርምር እንዲደረግ ምቹ ሁኔታ የመፍጠር፤

5/ የፓራሊምፒክ መሰረታዊ ጽንሰ ሀሳቦች በየደረጃው በሚገኙ የትምህርት ተቋማት ውስጥ በሚሰጥ የስፖርት ሳይንስ ትምህርት ውስጥ ለማካተት የሚያስችል ስልት የመቀየስ፤

6/ የዓለም አቀፍ ፓራሊምፒክ ኮሚቴ ቻርተርና ሌሎች ደንቦችን አክብሮ የመንቀሳቀስ፤

7/ ስፖርቱን የሚመለከቱ መረጃዎችን የማሰባሰብ፣ የማደራጀት፣ የመተንተንና የማሰራጨት፤

8/ ስፖርታዊ ጨዋነት እንዲሰፍን በስፖርታዊ መርሆዎችና ሥነ-ምግባር ዙሪያ ስልጠና

6/ When there is confirmed current financial Account.

## 20. <u>Duties and responsibilities of the Ethiopian Paralympic Committee</u>

The Ethiopian Paralympic committee has the following duties and responsibilities:

1/ Implementing the national sport policy, strategy, programs, laws, rules and regulations;

2/ Promoting and Developing the Paralympic sport movements in the country;

3/ Insuring the benefit of the country through Increasing the participation of peoples with disability in national and International Paralympic sport games;

4/ Rendering Trainings and Facilitating to conduct Researches regarding the development and promotion of Paralympic sports in the country;

5/ Creating mechanisms for introducing Paralympic values at every level of educa-tional center curriculums;

6/ Implementing; Respecting the international Paralympic charter and memorandum of association;

7/ Collecting, Organizing, analyzing and distributing the sport related information;

8/ Rendering trainings regarding the Sport ethics, values and fair play to avoid sports

መስጠት ስፖርታ ጨዋነት ሲጣስ እርምጃ የመውሰድ፤

9/ የክልል የፓራሊምፒክ ስፖርቶችን አቅም የመገንባትና የመደገፍ፤

10/ የብቃት ደረጃ ያላቸው ፓራሊምፒክ ስፖርቶችን ለማፍራት የሚያስችል ዘመናዊ የስልጠና ስልት የመቀየስና ተግባራዊ የማድረግ ፤

11/ ቢያንስ በአመት አንድ ጊዜ የማህበሩን ጠቅላላ ጉባኤ ማካሄድ፤

12/ የፓራሊምፒክ ስፖርታዊ እንቅስቃሴ ምቹ የሆኑ የማዘውተሪያ ስፍራዎችና ማቴሪያሎች እንዲሟሉ ጥረት የማድረግ፤

13/ ዓመታዊ እቅድ አፈጻጸም ሪፖርት ለሚኒስቴሩ የማቅረብ፤

14/ ሀገራችን ያፀደቀቻቸውን የፀረ-ዶፒንግ ኮንቬንሽን እንዲታወቅና እንዲተገበር የማድረግ፤ በሚወጡ ህጎች የአበረታች ቅመሞችን አካተው የማውጣትና በስፖርት አበረታች ቅመሞች ዙሪያ በሚደረገው ምርመራና ቁጥጥር አስፈላጊውን ትብብር የማድረግ፤

15/ በስፖርት አበረታች ቅመሞች ዙሪያ አስፈላጊውን የትምህርትና ስልጠናና የህዝብ ንቅናቄ ስራዎችን ማከናወን፤

16/ በየስፖርት ዓይነቱ ፌዴሬሽኖችን መደገፍ እና ውድድሮችን ራሳቸው እንዲመሩ የማስቻል፣

17/ በሚመራው ኮሚቴ የሚነሱ ማንኛውም ክሶችና አቤቱታዎችን መርምሮ ውሳኔ መስጠት፤

18/ ሌሎች አላማውን ለማስፈጸም የሚረዱ ተግባራትን የማከናወን ያጠቃልላል፡፡

violence and taking measures when violated;

9/ Assisting and Building Capacity for regional Paralympic sports;

10/ Creating and implementin Modern/Scientific training mechanisms to produce competency level Paralympic sports;

11/ Conducting the general assembly meeting at least once in a year;

12/ Increasing efforts for securing sport facilities and equipment Availability for Paralympic sports;

13/ Presenting the annual work reports;

14/ Respecting and promoting the national Anti-doping laws, incorporating anti-doping issues by its directives and Cooperating to any movements of anti-doping investigation and testing;

15/ Rendering the necessary education, training and campaigning regarding Anti-doping;

16/ Capacity building and Assistance for federations to host competitions independently;

17/ Making decisions for any complaints and grievances raised under its Olympic committee;

18/ Implement other duties to meet its objectives.

## 21. የኢትዮጵያ ፓራሊምፒክ ኮሚቴ አባላት

የኢትዮጵያ ፓራሊምፒክ ኮሚቴ የሚከተሉት አባላት ይኖሩታል፡፡

1/ የክልሎች የፓራሊምፒክ ኮሚቴዎች፤

2/ በስፖርት ዓይነት ወይም በጉዳት ዓይነት ከሚኒስቴሩ ፈቃድ አግኝተው የተቋቋሙ አገር አቀፍ ፌዴሬሽኖችን፤

3/ ኢትዮጵያዊ የሆነ የዓለም አቀፍ ፓራሊምፒክ ኮሚቴ አባል፤

4/ ኢትዮጵያዊ የሆነ የአፍሪካ ፓራሊምፒክ ኮሚቴ አባል፤

5/ በዓለም አቀፍ ፓራሊምፒክ ጨዋታ ተሳትፎ ያቆሙ 2 የአትሌት ተወካዮች፡፡

## 22. የኢትዮጵያ ፓራሊምፒክ ኮሚቴ ጠቅላላ ጉባኤ ስብጥር

የኢትዮጵያ ፓራሊምፒክ ኮሚቴ ጠቅላላ ጉባኤ የሚከተለው ስብጥር ይኖረዋል፡፡

1/ በስፖርት ዓይነት ወይም በጉዳት ዓይነት ከሚኒስቴሩ ፈቃድ አግኝተው የተቋቋሙ አገር አቀፍ ፌዴሬሽኖች ተወካዮች፤/በድምጽ/

2/ ኢትዮጵያው የሆነ የአለም አቀፍ ፓራሊምፒክ ኮሚቴ አባል፤ /በድምጽ/

3/ ኢትዮጵያዊ የሆነ የአፍሪካ ፓራሊምፒክ ኮሚቴ አባል፤/በድምጽ/

4/ የክልሎች የፓራሊምፒክ ኮሚቴ ተወካዮች፤/በድምጽ/

5/ የኢትዮጵያ ፓራሊምፒክ ኮሚቴ ፕሬዝደንትና የሥራ አስፈጻሚ ኮሚቴ አባላት፤/በድምጽ/

## 21. Members of Ethiopian Paralympic Committee

Ethiopian Paralympic committee shall have the following members:

1/ Regional Paralympic committees;

2/ National federations established on the basis of disabilities or sport types;

3/ An Ethiopian citizen having membership title in international Paralympic committee;

4/ An Ethiopian citizen having membership title in Africa Paralympic committee;

5/ Two representatives of athletes retired after participation in international Paralympic game.

## 22. Composition of the Ethiopian Paralympic Committee General Assembly

The general assembly of the Ethiopian Paralympic shall consist of the following composition:

1/ Representatives of National federations established on the basis of disabilities or sport types (with vote);

2/ Representatives of an Ethiopian citizen having membership title in international Paralympic committee (with vote);

3/ Representatives of an Ethiopian citizen having membership title in Africa Paralympic committee (with vote);

4/ Representatives of Regional Paralympic committees (with vote);

5/ Ethiopian Paralympic Committee President and members of executive committee (with vote);

6/ የኢትዮጵያ መስማት የተሳናቸው ስፖርቶች ፌዴሬሽን ተወካይ፤/ያለ ድምጽ/

7/ የኢትዮጵያ ዩኒቨርሲቲዎች ስፖርት ማህበር ተወካይ፤ /ያለ ድምጽ/

8/ የሀገር አቀፍ ማህበረሰብ አቀፍ የጤና ስፖርት ማህበር ተወካይ፤/ያለ ድምጽ/

9/ ጠቅላላ ጉባኤ የተመረተ ኦዲተር፤/ያለ ድምጽ/

10/ በጠቅላላ ጉባኤ የተመረጡ በመስኩ የሰሩ የክብር አባላት፤/ያለ ድምጽ/

11/ የሚኒስቴሩ ተወካይ፤/ያለ ድምጽ/

12/ የኢትዮጵያ ስፖርት ሳይንስ ባለሙያዎች ማህበር ተወካይ፤/ያለ ድምጽ/

**23. <u>የኢትዮጵያ ፓራሊምፒክ ኮሚቴ ስራ አስፈፃሚ ቦርድ ምርጫ</u>**

የኢትዮጵያ ፓራሊምፒክ ኮሚቴ ስራ አስፈጻሚ ኮሚቴ አባላት ምርጫ በሚከተለው ሁኔታ ይመራል፡፡

1/ የእጩ አቀራረብ

በዚህ መመሪያ አንቀጽ 11 ን/አንቀጽ 1 ለሀገር አቀፍ ስፖርት ፌዴሬሽን ስራ አስፈጻሚ አባላት ዕጩ አቀራረብ የተቀመጠው ድንጋጌ እንደተጠበቀ ሆኖ፡-

ሀ) ለፓራሊምፒክ ኮሚቴ ሥራ አስፈጻሚ ኮሚቴ አባል መወዳደር የሚፈልግ ማንኛውም የአባል ፌዴሬሽን ፕሬዚዳንት በፌዴሬሽኑ አማካኝነት በእጩነት ይቀርባል፡፡

ለ) የክልል ፓራሊምፒክ ኮሚቴዎች ለፕሬዚዳንትነት 1 ለሥራ አስፈጻሚ ኮሚቴ አባልነት 1 ዕጩ ያቀርባሉ፡፡

6/ Representative of Ethiopian deaf sport federation (without vote);

7/ Representative of Ethiopian universities sport association (without vote);

8/ Representative of National Community Sport Association, (without vote);

9/ An Auditor nominated by general assembly (without vote);

10/ Honorary members assigned by general assembly on the basis of their experience in the field (without vote);

11/ Representative of the ministry (without vote);

12/ Representative of Ethiopian sport science professionals' association (without vote).

**23. <u>Election Procedures of Ethiopian Paralympic Executive Committee</u>**

The election of Ethiopian Paralympic executive committee members shall respect the following procedures:

1/ Assignment of candidate

Without prejudice to article 11 (1) of this directive:

a) All presidents of member federation of the committee are able to be assigned for the executive committee as candidate by their respective federations;

b) Regional Paralympic committees shall assign one candidate for president and one for executive committee;

ሐ) የፓራሊምፒክ ኮሚቴ አባል ፌዴሬሽን አንድ ዕጩ ተወዳዳሪ ለፕሬዚዳንትነት ወይም ለስራ አስፈጻሚ ኮሚቴ አባልነት ለይቶ ያቀርባል፡፡

2/ ስለምርጫ አፈጻጸም ሂደት

በዚህ መመሪያ አንቀጽ 11 ን/አንቀጽ 2 ለሀገር አቀፍ ስፖርት ፌዴሬሽኖች የተደነገገው የምርጫ አፈጻጸም ሂደት በፓራሊምፒክ ኮሚቴ ላይም ተፈጻሚ ይሆናል፡፡

3/ ድምጽ አሰጣጥ

ሀ) የፓራሊምፒክ ኮሚቴ አባል የሆኑ የሀገር አቀፍ ስፖርት ፌዴሬሽኖችን ፕሬዚዳንቶች አንድ አንድ ድምጽ ይኖራቸዋል፡፡

ለ) የዓለም አቀፍ ፓራሊምፒክ ኮሚቴ አባል የሆኑ አንድ ድምጽ ይኖራቸዋል፡፡

ሐ) የአፍሪካ ፓራሊምፒክ ኮሚቴ አባል የሆኑ አንድ ድምጽ ይኖራቸዋል፡፡

መ) በፓራሊምፒክ ስፖርት ውድድር ተሳትፈው ውድድር ያቆሙ የአትሌቶች ተወካይ አንድ አንድ ድምጽ ይኖራቸዋል፡፡

ሠ) የክልል ፓራሊምፒክ ኮሚቴ ፕሬዚዳንቶች አንድ አንድ ድምጽ ይኖራቸዋል፡፡

ረ) በመደበኛ ዓመታዊ ጠቅላላ ጉባኤ ላይ የኮሚቴው ሥራ አስፈጻሚ ኮሚቴ አባላት አንድ አንድ ድምጽ ይኖራቸዋል፡፡

ሰ) የስራ ዘመናቸውን የጨረሱ የስራ አስፈፃሚ ኮሚቴ አባላት በምርጫ ጊዜ ድምፅ መስጠት አይችሉም፡፡

ሸ) በጠቅላላው ጉባኤ አብላጫ ድምጽ ያመጣ ተመራጭ ሲሆን ስፖርት ማህበሩ ከዓለም

c) All member federations of the committee shall assign one candidate for presidency or executive committee;

2/ Election procedure:

Notwithstanding of article 11 (2) of this directive shall apply for Ethiopia Paralympic committee;

3/ Voting Procedure:

a) All Presidents of member federations shall have one vote;

b) Member of International Paralympic committee shall have one vote;

c) Member of Africa Paralympic committee shall have one vote;

d) Representative of retired athletes of Paralympic sport games shall have one vote;

e) Presidents of regional Paralympic committee shall have one vote;

f) Executive committee members shall have one vote during the annual regular meeting of the general assembly;

g) Retired members of executive committees shall have no voting right (without vote);

h) Candidate that obtains majority vote on the general assembly shall assume the position, details of election procedure

አቀፉ ኮሚቴው ጋር አገናዝቦ በሚያወጣው የምርጫ ህግ መሰረት የሚፈጸም ይሆናል፡፡

ቀ) ድምጽ ምስጥራዊ በሆነ መልኩ ይሰጣል፡፡

24. **<u>የኢትዮጵያ መስማት የተሳናቸው ስፖርቶች ፌዴሬሽን ዓላማ</u>**

የኢትዮጵያ መስማት የተሳናቸው ስፖርቶች ፌዴሬሽን ዓላማ፡-

ሀ) የዘር፣ የፆታ የቋንቋ፣ የኃይማኖት፣ የፖለቲካ ልዩነት ሳይደረግና መድልኦ ሳይኖር መስማት የተሳናቸው ኢትጵያውያን የሚሳተፉባቸውን ስፖርቶች በመላ አገሪቱ በማስተዋወቅ፣ በማስፋፋት፣ በማሳደግና ውጤታማ በማድረግ ማህበረሰቡን ተሳታፊና ተጠቃሚ ማድረግ፤

ለ) የኢትዮጵያ ስፖርት ፖሊሲ፣ አገር አቀፍና ዓለም አቀፍ የስፖርት ህጎች፣ ደንቦች፣ መመሪያዎች በአገሪቱ እንዲታወቅና እንዲተገበር በማድረግ የስፖርቱን ህልውና ማስጠበቅ፤

25. **<u>የኢትዮጵያ መስማት የተሳናቸው ስፖርቶች ፌዴሬሽን ማቋቋሚያ መስፈርት</u>**

መስማት የተሳናቸው ስፖርቶች ፌዴሬሽንን ለመመስረትና ህጋዊ ዕውቅና ለማግኘት የሚከተሉትን መመዘኛዎች መሟላት ይኖርበታል፡፡

1/ በሃገሪቱ መስማት ለተሳናቸው ማህበረሰብ ስፖርትን ለማስፋፋት ብቸኛ አላማ ያለው መሆኑ ሲረጋገጥ፣

2/ ከአገር አቀፍ የስፖርት ማህበራት መቋቋሚያ መመሪያና ዓለም አቀፍ ደንብ ጋር የተናበበ የራሱ የሆነ ግልጽ መቋቋሚያ ደንብ መኖሩ ሲረጋገጥና መመስረቻ ጽሁፍ ማቅረብ ሲችል፣

3/ ቢያንስ በ5 ክልሎች በፌዴሬሽን ደረጃ

will have designed by the committee in line with international Paralympic committee;

i) The vote is conducted by secret ballot.

24. **<u>Ethiopian Deaf Sports Federation Objective of the federation</u>**

Ethiopian Deaf Sports Federation Objective of the federation is

a) Promoting and developing of Sports for Deaf communities without discrimination on the basis of race, gender, culture, religion, political orientation and other reasons;

b) To safeguard sport by means of promoting, enforcing and implementing national and international sport policies, rules and regulations in the country.

25. **<u>Requirements for the establishment of Ethiopia Deaf Sports Federation</u>**

The following requirements shall be complied to establish Ethiopian Deaf Sports Federation;

1/ An exclusive objective to promote sport for deaf communities in the country;

2/ By laws approved consistent with national sport associations establishment directive and international rules;

3/ Admitted at least five regional federations as

የተደራጁ ማህበራት መኖራቸውን ሲረጋገጥ፣

4/ በቡድን ስፖርቶች ተደራጅተው በክልሉ ዕውቅና ተሰጥቷቸው ቢያንስ ከ3 ያላነሱ ክለቦች ሲኖራቸው ወይም

5/ በግል ስፖርቶች በክልል የተመዘገቡ ቢያንስ 75 ስፖርተኞች ሲኖራቸው፣

6/ ሀገር አቀፍ ደረጃ ፌዴሬሽኑ የሚያወዳድራቸው ቢያንስ 5 ክለቦች በቡድን ስፖርቶች ወይም 150 የተመዘገቡ ስፖርተኞች በግል ስፖርቶች መኖራቸው ሲረጋገጥ፣

7/ የስፖርት ልማት ፕሮግራም መኖሩ ሲረጋገጥ፣

8/ የሂሳብ አያያዝን ስርዓት የዘረጋ እና ኦዲትን በስራ ላይ የሚያውል መሆንኑ ሲረጋገጥ፣

9/ ጽሕፈት ቤትና የሰው ኃይል መኖሩ ሲረጋገጥ፤

**26.** <u>**የኢትዮጵያ መስማት የተሳናቸው ስፖርቶች ፌዴሬሽን ስልጣንና ተግባር**</u>

የኢትዮጵያ መስማት የተሳናቸው ስፖርቶች ፌደሬሽን የሚከተሉት ስልጣንና ተግባራት ይኖሩታል፡፡

1/ የሀገራቱን ስፖርት ፖሊሲ፣ ስትራቴጂ፣ ፕሮግራም፣ ሕጎች፣ ደንቦችና መመሪያዎችን ተግባራዊ ምድረግ፤

2/ መስማት የተሳናቸው የህብረተሰብ ክፍሎች በስፖርታዊ እንቅስቃሴ ላይ ያላቸውን ተሳትፎ በሀገር ውስጥ የማስፋፋትና የማሳደግ፤

3/ በአለም አቀፍና በሀገር ደረጃ በሚዘጋጀው መስማት የተሳናቸዉ ስፖርቶች ጨዋታዎች መስማት የተሳናቸዉ ሕብረተሰብ ክፍል እንዲሳተፉ ያደርጋል፤

members;

4/ Admitted at least three legally organized clubs in team sports in regions; or

5/ Admitted at least legally registered seventy-five athletes in individual Sports in regions;

6/ Admitted five clubs in team sports or one hundred fifty athletes in individual sports participating at national competition;

7/ Owning designed sport development program;

8/ Established system for auditing and book of account;

9/ Having secretariat office and necessary human power.

**26.** <u>**Power and duties of the Ethiopian deaf sports federation**</u>

